# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 207 ሚያዝያ 25 2004 ገጽ 1


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በተለያዩ መንገዶች ከወያኔ ጋር ሲፋለሙ የወደቁ ጀግኖችን መስዋዕትነት ያከብራል። የወደቁለት ዓላማ ግቡን እንዲመታ አጥብቆ ይታገላል። የኢትዮጵያ ህዝብም፤ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ፤ ተባብሮ መለስን በማስወገድ በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈኑባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ቆርጦ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ወታደሮች በአርሲ አሳሳ መሲጊድ ሙስሊም ምዕመናንና በአፋር ክልል ነዋሪዎች ላይ የፈጸሙት ጭፍጨፋ በማውገዝ ግንቦት 7ና ኦነግ መግለጫ አወጡ

ወያኔ በመላው አገሪቱ ዜጎች ላይ ተራ በተራ እየፈጸመ ያለውን ጭፍጨፋ በማውገዝ ንቅናቄያችን ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሰኞ ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ባወጣው መግለጫ፤ ህወሃት የዘር የበላይነትን ለማስፈን ባለው የቆየ አላማ ዜጎችን ከትውልድ ቀያቸው በማፈናቀል መሬታቸውን የመንጠቅና የዘር ማጥፋት ተግባሩ ቀጥሎበታል በማለት በቅርቡ የአማራ ተወላጆችን ከሚኖሩበት የደቡብ ክልል በገፍ ማባረሩ፤ በጋምቤላ፤ በአፋርና በአሳሳ አርሲ ሰሞኑን የተፈጸሙ ጭፍጨፋዎች ወያኔ አላማውን ለማሳካት የሚወስዳቸውን ጨካኝ እርምጃ አድማስና መጠን እያሰፋ መምጣቱን አመልካች ናቸው ብሎአል።

በአለም ላይ ሁለቱ የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ተቻችለው ለዘመናት በሰላም ከኖሩበት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነቺው አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ለፓለቲካ አላማ ሲባል መለስ ዜናዊ ሁለቱን ሃይማኖቶች እርስ በርስ ለማጋጨት የሚያደርገው አደገኛ እርምጃ አንሶ ላለፉት 3 ወራት የሙስሊሙ ህብረተሰብ ላነሳው የመብቱ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ባለፈው አርብ በአርሲ ዞን በአሰሳ ከተማ መስጊድ ለጸሎት በተሰበሰበው ህዝብ ላይ በተከፈተው የተኩስ እሩምታ 8 ሰላማዊ ዜጎች መገደላቸው፤ ብዙዎች መቁሰላቸውና ወደ እስር መጋዛቸው እጅግ አሳዛኝና ሊወገዝ የሚገባ ድርጊት መሆኑን ገልጾአል።

የአፋርን ክልል የወረረው ወታደር ሃይል በአንድ ወር ዕድሜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ከመሬታችን አንፈናቀልም በማለት ያንገራገሩትንና ቤቶቻቸውን ለማፍረስ የተሰማሩትን ቡልዶዘሮች ለማስቆም የተጋፈጡትን ዜጎች መግደሉን ያተተው የግንቦት 7 መግለጫ እርጉዞችንና ልጅ የሚያጠቡ እናቶችን ሳይቀር በጅምላ ወደ እስር ቤት ያጋዘው የመለስ ዜናዊ ጦር አሰቃቂ ድብደባ ከፈጸመባቸው የአፋር ተወላጆች መካከል በጠመንጃ አፈሙዝ ጡቷ ላይ ተመትታ ህክምና እርዳታ ሳታገኝ ከልጇ ተነጥላ እስር ቤት የታጎረቺውንና ደብዳቢዎቿ ባደረሱባት ጉዳት ለከፍተኛ ህመም ስቃይ የተዳረገቺውን ፋጡማ ሙሳ ከወያኔ የግፍ ሰለባዎች አንዷ መሆኗን በሃዘን አስታውሶአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## እንደ ወያኔ አይነቶቹ አምባገነን የአፍሪካ መንግሥታት በይስሙላ ምርጫ የስልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም የሚይደርጉት ጥረት ጊዜው የለፈበት መሆኑን አንድ ከፍተኛ የአሜሪካ ባለስልጣን ተናገሩ

ይህንን የተናገሩት በአሜሪካ የስቴቲ ዲፓርትመንት የአፍሪካ ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት ጆኒ ካርሰን ሲሆኑ የዩናይትድ ስቴትስ የአፍሪካ ፖሊሲ ዋነኛ ግብ የህግ የበላይነት የነገሰባቸው፣ ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩባቸው፣ ግልጽነት የሰፈነባቸው መንግስታትና የዜጎች ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን የሆነባቸው፣ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጉ ሀገሮች እንዲኖሩ ማገዝ ነው በማለት አገራቸው አሜሪካ ስለ ህግ የበላይነት እየደሰኮሩ ህግ በመጨፍለቅ የአገዛዝ ዕድሜያቸውን በጠምንጃ አፈሙዝ እያራዘሙ ባሉት የአፍሪካ አንባገነኖች ተስፋ መቁረጧንና ከአሁን ቦኋላ እንደበፊቱ በጉያዋ አዝላ የመቀጠል ፍላጎት እንደሌላት አስታወቁ።

ጆኒ ካርሰን ይህንን የገለጹት በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ውጪ ግንኙነት ኮሚቴ ፊት ቀርበው በሰጡት ገለጻ ሲሆን የአሜሪካ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትንና ተሳትፎን ለማጠናከር የሚደረገውን ጥረቶች መደገፉን መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል። በተለይም መልካም አስተዳደርን በመደገፍ፣ ፓርላማዎችን በማጠናከር፣ የፍትህ ስርዓቱን ይበልጥ በማጎልበት የሴቶችንና የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎዎችን የሚያበረታቱና ወጣቱ ትውልድ የጠቅላላው ሂደት አካል እንዲሆን የሚረዱ ጥረቶችን አብዝተን እንረዳለን ያሉት ጆን ካርሰን ሙስናን በመዋጋት ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያግዙ ጥረቶችንም በአዲስ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ እንዳለ ገልጸዋል።

ጆን ካርሰን ባደረጉት ንግግር አሜሪካ የውጪ ግንኙነትን አስመልክቶ ፕሬዘደንት ኦባማ ከአመት በፊት በአክራ ያደረጉትን ንግግር በመጥቀስ የአሜሪካንን ወቅታዊ አቋም አጠናክረዋል። እሳቸው እንዳሉት በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ብቃት ያላቸው፣ አስተማማኝና በግልጽነት የሚሰሩ ተቋማት ለውጤታማነት ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው - ጠንካራ ፓርላማ፣ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአራቱም ማዕዘናት በከፍተኛ ውጠረት ውስጥ ተዘፍቆአል

ዘርን መሰረት ባደረገ የመድልዎ ፖሊሲ አገሪቱን ለ21 አመታት በጠመንጃ ሃይል እየገዛ ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መሃል አገርን ጨምሮ በሁሉም አቅጣጫዎች በተቀሰቀሰ ተቃውሞ እየተናጠ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሱ መረጃዎች አመለከቱ።

በአገሪቱ ማዕዘናት በሙሉ ለተቀሰቀሱ ተቃውሞዎች ዋናው ምክንያት ዜጎች ከአያት ቅም አያታቸው ዘመን ጀምሮ በተከታታይ ትውልድ ከኖሩበት መሬታቸው በሃይል ተፈናቅለው በልማት ሥም ለህወሃት የጥቅም ሸሪኮችና ለውጪ ኢንቨስተሮች መስጠት የቀሰቀሰው ብሶት መሆኑ ታውቆአል።

በሰሜን ምስራቅ የአገራችን ክፍል በአፋር ከመሬታችን አንፈናቀልም ያሉ በርካታ ዜጎች ወያኔ ወደ ክልሉ ያሰማራውን ዶዘር አናንቀሳቅስም በማለት የወያኔን ትዕዛዝ ለማስፈጸም በስፍራው ከተመደበው የፌደራል ፖሊሲና ጦር ሰራዊት ጋር ግብግብ ገጥመዋል። ህዝቡን በፍርሃት ለማሸማቀቅና የመሬት ንጥቂያውን ተፈጻሚ ለማድረግ ፖልስ በርካታ ዜጎችን ያሰረና የገደለ ቢሆንም በነቂስ ወጥቶ ተቃውሞውን በመግለጽ ላይ ያለውን ህዝብ በሃይል ለመበተን የሚደረገው ጥረት የበለጠ መካረርን ስለፈጠረ የክልሉ ባለሥልጣናትና የበላይ አለቆቻቸው በሁኔታው ግራ መጋባታቸውን ውስጠ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ።

በሰሜን በኩል ደግሞ ለዘመናት ተከብሮና ተጠብቆ የኖረውን የዋልድባ ገዳም ይዞታን ለስኳር ምርት ለማዋል በወያኔው አባ ጳሃይዬ የተላለፈው ውሳኔ በመላው አገሪቱ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን ከመቀስቀሱም በላይ በድርጊቱ የተከፋው የሰሜን ጎንደር ህዝብ ከያለቤት ተጠራርቶ የገዳሙን ህሊውና ለማስከበር በእጁ የሚገኘውን ማንኛውንም ጦር መሳሪያ ፤ ዶማና ገጀራ ሳይቀር ታጥቆ ወደ ስፍራው እንደተመመ ታውቆአል። በሁኔታው የተደናገጠው የወያኔ ጦር ምንም እርምጃ ከመውሰድ መቆጠቡ የአገሪቷን ታሪክ ለማፍረስና ሃብቷን ለመቦጥቦጥ መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የደሃውን ልጅ አስታጥቀው በራሱ ወገኖች ላይ በማዝመት እስከ መጨረሻው እንዘልቃለን የሚሉት የቆየ ህልማቸው ህዝብ ቆርጦ ከተነሳ ባዶ መሆኑን የሚያጋልጥ እርምጃ ሆኖአል ተብሎአል።

በምእራብ በኩልም እንዲሁ በጋምቤላና በቤኔሻንጉል ጉሙዝ ከፍተኛ ውጠረት የነገሰ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች ባለፈው ቅዳሜ በጋምቤላ ክልል የወያኔ የጥቅም ሸሪክ በሆኑት ሼክ አላሙዲን ይዞታ በሆነው ሳውዲ ስታር እርሻ ውስጥ ተቀጥረው በሚሰሩ ሰራተኞች ላይ የህዝብ ወገኖች የወሰዱትን እርምጃ ይጠቅሳሉ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአማራ ጥላቻ የታወረው የመለስ ዜናዊ ቡድን በአማራ ተወላጆች ላይ እየፈጸመ ያለውን የማፈናቀል ተግባር እንደቀጠለበት ፍኖተ-ነፃነት ዘገበ

እንደ ጋዜጣው ዘገባ፤ በደቡብ ክልል በጉራ ፈርዳ ወረዳ ይኖሩ የነበሩ አማሮች ያለምንም ወንጀል ለአመታት ከኖሩበትና ንብረት ካፈሩበት መኖሪያቸው ”ወደ አገራችሁ ሂዱ” ተብለው በግፍ መባረራቸው የቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ ሳይበርድ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ይኖሩ የነበሩ የአማራ ተወላጆች በተመሣሳይ ሁኔታ ተባረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በሰሜን ጎንደር ዞን ሱዳን ድንበር አቅራቢያ በሚገኘው አርማጭሆ ወረዳ ውስጥ በ ኢብርሀጂራ አካባቢ በ እርሻ ሥራ ተሰማርተው ይኖሩ የነበሩ የአማራ ተወላጅ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸውን ተነጥቀው ሰሞኑን መባረራቸውን፤ የአካባቢውን አርሶአደሮች መግለጻቸውን ጋዜጣው ይፋ አድርጎአል።

በዘራቸው ምክንያት ብቻ እየታደኑ ሰርተው ከሚኖሩበትና ሃብት ካፈሩበት እንዲባረሩ እየተወሰደ ባለው እርምጃ የተበሳጩት አርሶ አደሮች፡- አገዛዙ አሁንም በአማራ ላይ ጣቱን እንደቀሰረ መሆኑን በምሬት መናገራቸውን ፍኖት ገልጿል።

በዚህ የግፍ እርምጃ ከተለያዩ ቦታዎች ከይዞታቸው እየተፈናቀሉ ያሉት የአማራ አርሶአደሮች ምንም መቋቋሚያ ስላልተሰጣቸው የከፋ ችግር ላይ እየወደቁ መሆናቸውን ያመለከተው ዘገባ ሰሞኑን ከአርማጭሆ አካባቢ የተፈናቀሉት አርሶ አደሮች፤ ከ1998 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በስፍራው ሲኖሩ የቆዩ መሆናቸውን እንደሚናገሩና ከይዞታቸው እንዲነሱ በሚደረጉበት ወቅት”መሬቱ በብሎክ ስለሚደለደል፤ ያለሰለስኩት ማሳዬ ስለሆነ ለኔ ይገባኛል “የሚል ጥያቄ እንዳያነሱ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸውም ገልጸዋል።

ከአርማጭሆ እየተፈናቀሉ ላሉት አርሶ አደሮቹ ዋናው ምክንያት ወያኔ አካባቢውን ቆርሶ ለሱዳን ለመሰጠት በመወሰኑ እንደሆነ ተገልጿል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የሰማዕታት ደም ፈሶ አይቀርም!!!

የያዝነው ሳምንት የመለስ ዜናዎች ፋሽስታዊ አገዛዝ የፈጠራቸው ብዙ ሃዘኖችና መከራዎች ኢትዮጵያዊያን ላይ የተፈራረቁበት ሳምንት ነው። እነዚህ የሚያስቆጩና የሚያንገበግቡ ጥቃቶች የተፈጸሙባቸውን ቦታዎች ለማጤን የሞከረ ሰው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ክፋት ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ጫፍ፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ መላውን የአገራችንን ክፍል ያዳረሰ መሆኑን ይረዳል።

ለአብነት የሚከተሉትን እንጥቀስ።

- ሚያዚያ 16 ቀን በፍትህ እጦትና በኑሮ ውድነት የተማረረ አንድ ወጣት መሃል አዲስ አበባ ውስጥ ራሱን በራሱ በእሳት አጋየ። ስሙ ዳዊት ከመሰኘቱ እና የፓሊስ ሠራዊት አባል የነበረ ከመሆኑ በላይ ስለዚህ ዜጋ ብዙ አይታወቅም። ዜናውን ለመከላከል ሲሉ የመለስ ዜናዊ ሰላዮች ክፉኛ የቆሰለውን ወጣት አፍነው ይዘዋል።
- ሚያዝያ 19 በአርሲ ዞን አሳሳ ከተማ የፌደራል ፓሊሶች በሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ላይ በፈጸሙት ጭፍጨፋ የስድስት ዓመት ህፃንን ጨምሮ ሰባት ሰዎች ገድለው በርካቶችን አቁስለዋል። የእነዚህ ምዕመናን ጥፋት “ወያኔ በሃይማኖታችን አይግባብን፣ የሃይማኖት መሪዎቻችንን ራሳችን እንምረጥ፣ ሲቢክ ማኅበሮቻችን በነፃነት ይንቀሳቀሱ” ብለው መጠየቃቸው ነው።
- ሚያዝያ 19 ቀን በአፋር ክልል በዱብቲ ከተማ መሬት ለባዕዳን ቱጃሮች መንደላቀቂያነት አልሰጥም ባለው በአፋር ህዝብና በወያኔ መካከል በተፈጠረው ግጭት ሰበብ የመለስ ጦር ወታደሮች የ17 አመቱን አሊ ኡመር ሙሀመድን ገድለዋል፤ ሴቶችና ህፃናትን ጨምሮ በርካታ ዜጎችን አቁስለዋል፤ ደብድበዋል።
- በሺዎች የሚቆጠሩ የጎንደር ክርስቲያን ምዕመናን ደግሞ የዋልድባ ገዳማትን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከል ፊት ለፊት ተፋጠዋል። እስካሁን በዚሁ ቅራኔ ሳቢያም ሁለት የውጭ አገር ዜጎች መሞታቸው ተዘግቧል።
- የጋምቤላን ለም መሬት በገፍ ተሰጥቶት፤ የአባቢውን ነዋሪዎች አፈናቅሎ በዘመናዊ ግብርና ሃብት እያጋበሰ ላለ የውጭአገር ባለሃብት ተቀጥረው ከሚሰሩት ውስጥ አንድ ፓኪስታናዊ እና አምስት ኢትዮጵያዊያን በታጣቂዎች ተገድለዋል፤ ተጨማሪ አራት ፓኪስታናዊያንና አምስት ኢትዮጵያውያን ቆስለዋል።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የተፈጸሙ ነገሮች ናቸው። ምሬት ኢትዮጵያን ከጫፍ እጫፍ አዳርሷታል። ሙስሊሙም ክርስቲያኑም፤ ቆለኛውም ደገኛውም በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ተማሯል። የገዛ ራሳቸውን በእሳት የሚያጋዩ ወጣቶች መብዛት የምሬቱ ጥልቀት ገላጭ ነው። በራስ ተነሳሽነት እርምጃ መውሰድ መጀመሩም የሕዝባዊ አመጽ መዳረሻ ላይ መሆናችንን ያበስራል።

እናም በዚህ ሁሉ አፈናና ምሬት ውስጥ ጭላንጭል ይታያል። የሰማዕታት ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም። የክርስቲያንም የሙስሊምም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም። መሃል ፒያሳ ላይ ራሱን ያጋየው ወጣት መስዋትነትም ፍሬ ማፍራቱ አይቀርም።

ዛሬ “ሰው ያለ ነፃነት ምኑን ሰው ይባላል?” እያሉ ቁርጠኛ ውሳኔ የሚወስዱ ዜጎች ቁጥር ተበራክቷል። ስለሆነም ምንም እንኳን ሳምንቱ ሃዘን የበዛበት ቢሆንም በኢትዮጵያ ሕዝብ መነሳሳት ምክንያት መጽናናትን እናገኛለን። እነዚህ ኩነቶች መለስና ቡድኑ ከኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ላይ የሚራገፉበት ወቅት መድረሱን አመላካች ናቸው። ፍርሃት እየተናደ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በተለያዩ መንገዶች ከወያኔ ጋር ሲፋለሙ የወደቁ ጀግኖችን መስዋዕትነት ያከብራል። የወደቁለት ዓላማ ግቡን እንዲመታ አጥብቆ ይታገላል። የኢትዮጵያ ህዝብም፤ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ፤ ተባብሮ መለስን በማስወገድ በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈኑባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ቆርጦ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

**ክብር ለሰማዕታት!!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ወታደሮች በአርሲ አሳሳ መሲጊድ ሙስሊም ምዕመናንና በአፋር ክልል ነዋሪዎች ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከመሬታችን አንፈናቀልም በማለት ቤታቸውን በሃይል ለማፍረስ የተሰማራውን ዶዘር ለማስቆም እየተጋፈጡ ያሉት የአፋር ወገኖቻችን፤ መብታቸውን ለማስከበት ቻይና ውስጥ በ1989 ዓም በታይናነመን አደባባይ ተደርጎ የነበረውን ሰላማዊ ሰልፍ ለመበተን ከተሰማራው የቻይና ታንክ ጋር በመጋፈጣቸው አለም አቀፉ እውቅናና ድጋፍ ከተቸሩት የቻይና ነጻነት ታጋዮች ያልተናነሰ ትግል እያካሄዱ በመሆናቸው አለም አቀፉ ህብረተሰብ ጆሮውን ሊሰጠውና ድጋፉን ሊገልጽ ይገባል ያለው የግንቦት 7 መግለቻ የወያኔን የመሬት ቅርምት ፖሊሲ በመቃወም በኦሮሚያ ፤ በአፋር በጋምቤላና በቤኔሻንጉል ጉሙዝ ዜጎች ተቃውሞዋቸውን በተለያየ መንገድ እየገለጹ መሆናቸውን ጠቅሶአል።

በመጨረሻም ግንቦት 7 መላው ህዝባችን የሙብት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ የወያኔ ጥቃት ሰላባ ከሆኑት የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጎን እንዲሰልፍና የአፋር ወገኖቻችን ለአገር ባሌቤትነት ለነጻነትና ለክብራቸው እያደረጉት ያለውን ትግል እንዲደግፍ ጥሪውን በማቅረብ የአለም አቀፉ ህብረተሰብ በተለይም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ የአሜሪካና የአውሮጳ መንግሥታት እንዲሁም የሰብ አዊ መብት ተሟጋቾች በአፋርና በአርሲ አሳሳ ሙስሊም ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ እንዲያጣሩ ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የአዲስ አበባው አገዛዝ ዘጎችን በዘርና በሃይማኖት እየከፍፈለ በመፈጸም ላይ ካለው እኩይ ተግባሮች እንዲታቀብ ጫና እንዲያደርጉ ጥሪውን አቅርቦአል።

ይህ በ እንዲህ እንዳለ በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በበኩሉ የወያኔው አገዛዝ በአርሲ ዞን በአሳሳ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው ግዲያ አካል ነው በማለት መግለጫ አውጥቶአል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በአርሲ ዞን በአሳሳ ከተማ ለአርብ ጸሎት በወጣው ህዝብ ላይ የወያኔ ፈደራል ጦር ያደረሰውን ጭፍጨፋ የሰማው በታላቅ ድንጋጤ ነው ያለው የኦነግ መግለጫ መለስ ዜናዊ ከሳምንት በፊት ለፓርላማ ባደረገው ንግግር የአልቃይዳ ህዋስ በአርሲና በባሌ መኖሩን እናውቃለን በማለት የፌጠራ ውንጀላ ሲያቀርብ በኢስልምና አክራሪነት ሰበብ አሁን የወሰደውን አይነት ጭፍጨፋ በኦሮሞዎች ላይ ለማድረስ ዝግጅት እንዳለው አመልካች ነበር ከዚህም በመነሳት ይህ የአሁኑ እርምጃ የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እንዳማይሆን መገመት አያስቸግርም ብላአል።

የአምልኮ ነጻነት በይስሙላው የወያኔ ህገመንግሥት ሳይቀር እውቅና ያገኘ መብት ሆኖ ሳለ ዜጎችን በአምልኮ ቦታቸው መጨፍጨፍ የባሰ የሰባዊ መብት ጥሰት ነው የሚለው ኦነግ በዚህ ኢሰባዊ ድርጊት መለስ ዜናዊ ለአለም አቀፍ ፍርድቤት መቅረብ ይኖርበታል ብሎአል።

ከዚህ በተጨማሪ የወያኔው አገዛዝ ለዘመናት በሰላም ተከባብሮና ተፋቅሮ የሚኖረውን የወሊጋ ና የቤነሻንጊል ህዝቦችን ሆን ብሎ ለማጋጨትና ደም ለማቃባት እያደረገው ያለው ተንኮል ህዝቦች ለጋራ ጥቅማቸውና ለመብታቸው ወያኔ አገዛዝ ላይ በአንድነት መነሳታቸው አሳስቦት ስለሆነ ሁሉም ሁሉም የአገራችን ህዝብ ይህንን መሰሪ ተንኮል በጽኑ እንዲኮንንና እንዲያመክን ሃላፍነት አለብት ብላአላ የኦነግ መግለጫ።

በመጨረሻም በአሳሳ የተፈጸመው ጭፍጨፋ የወያኔው አገዛዝ እየፈጸመ ያለውን አሰቃቂ የሙብት ጥሰቶች ገላጭ ከመሆኑም አልፎ ጊዜ ከተሰጠው ሃይማኖትን በሃይማኖት ላይ በማነሳሳት የከፋ እልቂት ለማምጣት የታሰበ መሆኑ ግንዛቤ አግኝቶ እያንዳንዱ የኦርሞ ተወላጅና መላው ኢትዮጵያዊ ድርጊቱን በጽናት ከማውገዝ ባሻገር ወያኔ ከደገሰልን መተላለቅ ህዝባችንንና አገራችንን ለመታደግ እንድንችል ሁላችንም እጅ ለ እጅ ተያይዘን መነሳት ይኖርብናል በማለት አለም አቀፍ ኮሚኒቲውም በአሰሳ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ እንዲያወግዝና እንዲህ አይነት ወንጀል እንዳይደገም ከኛ ጋር እንዲሰልፍ ጥሪውን አቅርቦአል።

## እንደ ወያኔ አይነቶቹ አምባገነን የአፍሪካ መንግሥታት በይስሙላ ምርጫ የስልጣን ዕድሜያቸውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለህገ መንግስት ታማኝ የሆነ ፖሊስ፣ ነጻ የፍትህ ስርዓት፣ ነጻ ፕሬስ፣ ጠንካራ የግል ሴክተርና የሲቪል ህብረተሰብ ነበር ያሉት ኦባማ። የዘመኑ ታሪክ ከጠንካሮቹ የአፍሪካ ህዝቦች ጎን ነው፤ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ህገ መንግስት ለሚቀይሩና ሌሎችንም ስልቶች ለሚጠቀሙ አምባገነኖች ግን አልፎባቸዋል። ምክንያቱም አፍሪካ ዛሬ ጠንካራ ገዢዎች ሳይሆኑ ጠንካራ ተቋማት ናቸውና የሚያስፈልጓት በማለትም አጽንዖት ሰጥተውታል።

አፍሪካ በአሁኑ ወቅት በግልጽ የታወቁ ችግሮች ያሉባት ቢሆንም ፕሬዘደንት ኦባማ፣ የውጪጉዳይ ሚኒስትር ክሊንተን፣እኔም ሆንኩ ሌሎች አፍሪካና አፍሪካዊያን እነኚህን ችግሮች ተቋቁመው በአሸናፊነት እንደሚወጡ ሙሉ እምነት አለን ብለዋል።

አሁን አሁን የአፍሪካ ወጣት ትውልድ በዕውቀት እየደረጀ እንደመምጣቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥያቄዎችን እያነሳ ነው።በመሆኑም በተለይ ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት ውስጥ በአዲሱና በአሮጌው አምባገነን ኋለ ቀር አስተሳሰብ መካከል ውጥረት እየተባባሰ ነው ያሉት ካርሰን የዩናይትድ ስቴትስ የአፍሪካ ፖሊሲም አይቀሬውን ለውጥ በአፍሪካ ከግምት ያስገባ ነው ሲሉ አክለዋል።

ካርሰን በማያያዝም ዴሞክራሲ በህዝብ፣ ከህዝብ፣ ለህዝብ የሆነ መንግስት ማለት ነው። ይህ ደግሞ የዕጩነትና የምርጫ ጨዋታ ሳይሆን ዜጎች የሚሳተፉበት ፣የሚመርጡበትና የሚመረጡበት ሥርዓት ነው። ምክንያቱም የማንኛውም ጠንካራ ዴሞክራሲ መሰረቱ የዜጎች የስልጣን ባለቤትነት ነውና በማለት አብራርተዋል።

እንደፈረንጆች አቆጣጠር አፕሪል 18 ቀን በስቴትስ ዲፓርትመንት የተሰጠው ምስክርነት አሜሪካ እንደመለስ ዜናዊ ሥልጣን ላይ ለ21 አመት በቆዩት አምባገነኖች ላይ ያላትን ተስፋ መቁረጥ የሚያመለክቱና የፖሊሲ ለውጥ አስፈላጊነት የግድ እያለ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን የፖለቲካ ጠበብት ተናግረዋል።

## መለስ ዜናዊ የዘመናችን መርገምት!!!

በመለስ ዜናዊ ዙሪያ ከተሰባሰቡ ዘረኞችና ዘራፊዎች መካከል አንዱ ድምጹን ከፍ አድርጎ "ዋልድባ የትግራይ ሃብት ስለሆነ ሌላው በውስጥ ጉዳያችን ምን አገባው" ማለቱን ሰማን። ይህ የደረስንበትን የመርገምት ደረጃ የሚያመላክት ነው። እንዲህ ያለ እርግማን የሚሰማው በመለስ ዜናዊ የአገዛዛ ዘመን እንጂ በሌላ በማንም ዘመን እንዲህ ያለ ነውር ተሰምቶ አይታወቅም።

የህወሃት ነውር ብዙ ነው።

የጠላት አገር የወረሩ ይመስል በየከተማው ያገኙትን ምናምኑን የቻሉትን ያህል ነቅለው መውሰዳቸውን እናስታውሳለን። አሁን ደግሞ ራስ ደጀን ተራራ ያለው ጎንደር ውስጥ ሳይሆን ትግራይ ውስጥ ነው ብለው ትውልዱን ሃሰት ትምህርት ሊያስተምሩት ጀምረዋል። ይሄም ሌላው የዘመናችን መርገምት ነው። እንዲህ ያሉ መርገምቶች ለምን ተብለው በህዝቡ መካከል እንዲሰራጩ እንደሚደረግ እኩዩ መለስም ሆነ በዙሪያ የተሰባሰቡ ዘባተሎዎች  ሂሊናቸው ሊያስበው  ደግነትን አጥቷል።

ራበን፤ ልጆቻችንን መመገብ ተሳነን፤ ቤታችንም ሃዘን በዛበት፤ መንግስት በልተን ማደር የምንችልበትን መንገድ ይፈልግልን ብለው የተማጸኑ መምህራንን "ችሎታ የሌላቸው ደካሞች" ብሎ መለስ ዜናዊ መሳደቡም ሌላው የዘመኑ መርገምት ነው። በአገሪቷ ውስጥ መልካምን ዘር የሚዘሩ መምህራን በኑሮ ውድነት የተነሳ መኖር ተስኖናልና ደመወዛችንን ጨምሩ ብለው በመጠየቃቸው ብቻ "ችሎታ የሌላቸውና ደካሞች"ተብለው መሰደባቸውን በሰማን ግዜ ሃዘኑ ውስጣችን ድረስ ዘልቆ ገብቷል። መምህራኑ ኑሮ ስቃይ ሆኖባቸው በሞትና በህይወት መካከል ሲያጣጥሩ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ ከአገሪቷ ላይ ሰርቀው በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ መደበቃቸውን የነገረን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንጂ ሌላ አይደለም። ከዚህ ገንዘብ ላይም የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን በአንድ ቀን ብቻ አንድ ሚሊዮን ዶላር አውጥታ የምትጌጥበትን ልብስ መግዛቷን ብዙ መገናኛ ብዙሃን መዘገባቸውን ሰምተናል። አገሪቷን እየዘረፉ  ድሆችን የሚያስለቅሱ የኤልዛቤልን መንፈስ የተላበሱ ነውረኞችን  በዚያች ድሃ አገር ውስጥ ማየት በአገራችን ላይ የተተከለ መርገምት ነው እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል ?

በመለስ ዜናዊ ዘመነ አገዛዝ ያላየነው የመርገምት ዓይነት የለም።የሰው ልጅ ከአንድ ዛፍ አንሶ ከኖረበት ተነቅሎ ሲጣል ያየነው በመለስ ዜናዊ ዘመን ነው። ከጉራፋርዳ ወረዳ ዛፍ ቆርጣችኋል ተብለው ከኖሩበት ተነቅለው ሜዳ ላይ የተጣሉት አማሮች ጩኸታቸውን የሚሰማ ጠፍቶ የትም ተጥለዋል።የሰው ልጅ ከአንድ ዛፍ አንሶ ከሥሩ ተነቅሎ ከነ ልጆቹ ሜዳ ላይ ሲጣል ማየትና መስማት ለኢትዮጵያዊያን ከባድ ፈተና ሁኗል።ኢትዮጵያዊው ከማሳው ላይ ተነቅሎ የትም ተጥሎ መሬቱ ለህንድ፤ ለፓኪስታን፤ ለአረብ ሲታደል ማየት ለኢትዮጵያዊያን መርገምት ነው። በሺዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን ከቀያቸው ነቅሎ ሜዳ ላይ በትኗቸው ሲያበቃ የተፈናቀለ ምንም "ሰው" የለም ማለቱን በሰማን ግዜ መለስ ዜናዊ "ይህች አገር" እያለ ለሚጠራት ኢትዮጵያና ለህዝቧ ያለውን ጥልቅ ጥላቻ በተግባር እያሳየን መሆኑን ዜጎች ልብ ልትሉ ይገባል። መሬታቸው ተነጥቆ ለአረብ ለህንድና ለመሳሰሉት ከታደለ በኋላ ማረፊያ  አጥተው ሜዳ ላይ የተበተኑት ዜጎች በመለስ ዜናዊ አይን "ሰዎች" አይደሉም።ስለዚህ መለስ ዜናዊ ድምጹን ከፍ አድርጎ የተፈናቀለ ሰው የለም ማለቱ አገራችን ያለችበትን የመርገምት ዘመን የሚያሳይ ተጨማሪ ጉዳይ ነው።

የህወሃት ሹመኞች በደቡቡና በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ለዘመናት የኖሩትን ዛፎች እንደ ጠላት ገንዘብ ቆጥረው ጨፍጭፈው ሸጠው ስም አጠራሩን እንኳ የማያውቁትን አልኮሆል እየተጋቱ ሲሞላቀቁበት በዓይናችን አይተናል በጆሮአችንም ሰምተናል።እነርሱ የአገሪቷ ውበት የሆኑ ደኖችን ሲጨፈጭፉ የሚያወድሙት የጠላት ንብረት ነውና በጎ አደረግን ይላሉ፤ የኢትዮጵያ ድሃ ገበሬ ግን ቤተሰቡን  ለመመገብ ዱር ገብቶ ጫካ ሲመነጥር ወንጀለኛ ተብሎ ከቀየው ተነቅሎ የትም ይጣላል።በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወደር የማይገኝለትን በደል በገዛ አገራችን ሲፈጸም ያየነው በዘረኛውና በዘራፊው መለስ ዜናዊ ዘመነ መንግስት እንጂ በሌላ በማንም አይደለም።

በዚህ ዘመን እነመለስ ዜናዊ የፈጠሩት መርገምት ብዙ ነው።ስኳር ተወዶ ህዝቡ ሲጮኽ መለስ ዜናዊ "የስኬታችን አንዱ መለኪያ በመሆኑ እንኮራለን" ማለቱን ሰምተናል። ስኳር ቀምሶ የማያውቀው ገበሬም ስኳር ስለቀመሰ እንኮራለን እንጂ አናፍርበትም ማለቱን በሰማን ማግስት ገበሬውን እያፈናቀሉ መሬቱን ለባእዳን ሸጠው ሜዳ ላይ ሲበትኑት ማየት ሌላው መርገምት ነው።

የአገራችንን መከራ ለማብዛት ቆርጠው የቆሙት እነመለስ ዜናዊ በፈጠሩት የኑሮ ውድነት ምክንያት የአንድ ኪሎ ቡና ከ180 ብር በላይ በመግባቱ በኢትዮጵያችን ምድር ቡና የቅንጦት መጠጥ ሁኗል። እንዲህ ሲሆን 10,000 ቶን  ወይም 9 ሚሊዮን ኪ.ግ ቡና  የደረሰበት ጠፍቷል።መለስም ቡናው የደረሰበትን እናፈላልግ ሲባል ፍለጋ እንዳይደረግ አድርጓል። ምክንያቱ አንድና አንድ ነው። አስር ሺህ ቶን ቡናውን በጠራራ ጸሃይ የሰረቁት ራሱ መለስ ዜናዊና የኤልዛቤል መንፈስ ነች በመባል የምትታወቀው ሚስቱ አዜብ በመሆናቸው ነው።ከዚያ ግዜ በኋላ የቡና ዋጋ ለድሃው ኢትዮጵያዊያ የማይቀመስ በመሆኑ ቡናን እንደ ልባቸው የሚጠጡት በመለስ ዙሪያ የተሰባሰቡት ዘራፊዎችና ዘረኞች ብቻ ሆነዋል።መለስና ግብረ አበሮቹ እንዲህ እያደረጉ የዜጎችን ስቃይ ሲያበዙት እያዩ ዝም የሚሉ ከንቱ ግለሰቦች መኖራቸውም በራሱ መርገምት ነው።

ኢትዮጵያዊያን ሆይ በዚህ ዓይነቱ መርገምት ውስጥ አንገታችንን ደፍተን እንድንኖር ክብራችን አይደለም። ይህንን መርገምት ከአገራችን ነቅለን ለመጣል ከእንግዲህ ስንት ግዜ ያስፈልገናል? በእነዚህ ነውረኞች እጅ ወድቀንና ጎራ ለይተን እርስ በርሳችን ተለያይተን ይህን መርገምት ከአገራችን ለመንቀል ይቻለናልን ?ዛሬ የዋልድባ መነኮሳት ጥያቄ ጥያቄያችን ሊሆን ይገባል። የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ ጥያቄያችን ሊሆን ይገባዋል።የጋምቤላ ህዝብ ጥያቄ ጥያቄያችን ሊሆን ይገባል።የአዲስ አበባ ወጣቶች ጥያቄ ጥያቄችን ሊሆን ይገባል። በአሩሲ የተነሳው ጥያቄ ጥያቄያችን ሊሆን ይገባል። ከእነዚህ ወገኖች የተነሱትን ጥያቄዎች አብረን አንስተን በአገሪቷ ላይ የተተከለው መርገምት እንዲነቀል መለስ ዜናዊ ከተቆናጠጠበት ወንበር እንዲወረድ ለማድረግ ግዜው አሁን ነው።አገራችን ከዚህ በላይ መለስ ዜናዊን የመሰለ እርግማን ይዛ ልትቀጥል አትችልም። ግዜው አልፏል። አሁን በቃ።

ግንቦት ሰባት ንቅናቄ ያነሳው የፍትህ፤ የእኩልነት፤ የነጻነትና የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥያቄ በአግባቡ እስኪመለስና ዜጎችን በየሜዳው ገለው የጣሉ ወንጀለኞች ለፍርድ እስከሚቀርቡ ድረስ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል። በህዝቦች መካከል የሚታዩት ልዩነቶችን የውበታችንና የኃይላችን መገለጫዎች አድርጎ ይጠቀመዋል እንጂ የሽንፈታችንና የውርደታችን ምክንያቶች እንዲሆኑ አያደርግም። በእኛ እምነት በዚህ ውበታችን ታጅበን፤ ልዩነታችን የሚሰጠንንም ኃይል ተጠቅመን ይሄን መርገምት ከአገራችን ነቅለን ለመጣል የምንችለውን ለማድረግ እየሰራን ነው።በዚህ ትግል ውስጥ ኢትዮጵያዊነቱን የሚወድ ሁሉ መሳተፍ አለበት። በዚህ የመርገምት መዓት ውስጥ እጅና እግሩን አጣጥፎ የሚቀመጥ መርገምቱን ካመጡብን ቡድኖች በምን እንደሚለይ ራሱን ይመርምር። እግዚአብሄር አገራችንን ይባርክ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

---

## በአማራ ጥላቻ የታወረው የመለስ ዜናዊ ቡድን በአማራ ተወላጆች ላይ እየፈጸመ ያለውን የማፈናቀል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከዚህም ባሻገር፤ በታች አርማጭሆ ወረዳ፤ ሳንጃ ውስጥ ለረጂም ዓመታት የቤተ-ክርስቲያን መገልገያ የሆነን ሥፍራ "ለልማት" ተብሎ ለአንድ ባለሀብት እንዲሰጥ በመወሰኑ፤ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ መፈጠሩን  ጋዜጣው ጨምሮ ዘግቧል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብ በውሳኔው መቆጣቱ ያሣሰባቸው  የወረዳው ኃላፊዎች ህዝቡን ሰብስበው ለማግባባት ቢሞክሩም ህዝቡ በተቃውሞው በማምረሩ በአካባቢው ውጥረት መንገሱን  ነዋሪዎቹ ተናግረዋል፡፡ አካባቢው፤ በምርጫ 97 ወቅት ወያኔ ኢህአዴግ አንድም ድምጽ ያላገኘበት አካባቢ በመሆኑ፤ ነዋሪው በተለይ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ባሉት  ዓመታት ከፍ ያለ አስተዳደራዊ በደል ሲፈጸምበት መቆየቱን የዜናው ምንጮች አስታውሰዋል።

"በአሁኑ ጊዜ የአካባቢውን ህብረተሰብ ነፃነቱ ሙሉ በሙሉ ተገፏል፤ ሁሉም ዜጋ የቁም እስረኛ ተደርጓል፡፡ ከሚኖርበት ቀበሌ ወደ ሌላ ማናቸውም ቀበሌ ለመሄድ ቢፈልግ እንኳ፤ ለአካባቢው ኃላፊዎች አሳውቆ የይለፍ ወረቀት መያዝ ይጠበቅበታል ተብሎአል፡፡

የፍቃድ ወረቀት ሳይኖረው ከሚኖርበት ቀበሌ ተነስቶ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመሄድ የሚሞክር ማንኛውም ዜጋ  እንደሚታሰር የሚናገሩ የአካባቢው ምንጮች በህዝቡና በአገዛዝ መካከል ከፍተኛ የሆነ ፍጥጫ መፈጠሩንና በዚህም የተነሳ ውጥረት በአካባቢው መስፈኑን ይናገራሉ።

## የወያኔ የይስሙላ ፍርድ ቤት ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን በ2 ሺ ብር ሲቀጣ . . . (ከገፅ 4 የዞረ)

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ለአንድ ሰዓት ያህል በፍርድ ቤቱ ውስጥ በሚገኘው ጊዜያዊ የእሥረኞች ማቆያ የብረት ፍርግግ ውጥ በቁጥጥር ሥር ውሎ የሥራ ባልደረቦቹ ሁለት ሺህ ብሩን በባንክ ሲፒኦ አስገብተው ሲያጠናቅቁ ተፈቷል፤ በርካታ ሰዎችም መፈታቱን ሲጠባበቁ ተስተውሏል፡፡

ከንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ዓርብ ሚያዚያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም "ማቆሚያና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ እንባ" በሚል በፍትህ ጋዜጣ የወጣው ጽሑፉ የእርሱ ስለመሆኑ እንዲያሰድረዳ ችሎት እንዲቀርብ በተደረገበት ጊዜ "አዎን! በጋዜጣው ላይ የፃፍኩት የእኔን የግል እምነትና አስተሳሰብ ነው የምጠየቅበትም ከሆነ እኔ ልጠየቅ" ማለቱ ይታወሳል፡፡

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአራቱም ማዕዘናት በከፍተኛ ውጠረት ውስጥ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በደርግ ዘመን ከህዝብ በተሰበሰበ ግብር የባሮ ወንዝ ላይ ለምቶ የነበረውን ሰፊ የእርሻ መሬት ህወሃት ለራሱ ምርጦ ሰዎችና ለሼክ አላሙድን ካከፋፈለ በኋላ በደን ተሸፍኖ የኖረውን ሌላ ሰፊ መሬት ለህንድና ለአረብ ከበርቴዎች በርካሽ ዋጋ መቸብቸቡን የተቃወሙ የክልሉ ነዋሪዎች መሳሪያ በማንሳት ላለፉት 4 ወራት ወያኔን በመፋለም ላይ ይገኛሉ።

ባለፈው ቅዳሜ የሼክ አላሙድን ሳውዲ ስታር እርሻ ላይ በሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ጥቃት የከፈቱት የአካባቢው አማጽያን አራት ኢትዮጵያውያን እና አንድ ፓኪስታናዊ መገደላቸውን እንዲሁም አራት ፓኪስታናውያንና 5 ኢትዮጵያውያን መቁሰላቸውን ተከትሎ፣ በሼክ ሙሀመድ ሁሴን አል አሙዲን ሳውዲ ስታር ኩባንያ ውስጥ በከፍተኛ አመራርነት ይሰሩ የነበሩ ከ70 በላይ የፓኪስታን ዜጎች አካባቢውን ለቀው ወደ አዲስ አበባ መጓዛቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

ዜጎችን በማፈናቀል የጋምቤላን መሬት ለተቀራመቱ የህወሃትና የውጪ ባለሃብቶች ጥበቃ በክልሉ የተመደበው የመከላከያ ሰራዊትና  የክልሉ ባለስልጣናት ባለፈው ሰኞ ህዝቡን ሲያነጋግሩ እንደነበረ የገለጹት ምንጮች ባለስልጣናቱ " አማጽያኑን እናንተ አጋልጣችሁ ካልሰጣችሁን እኛ በራሳችን የደህንነታችሁን ዋስትናችሁን ለማረጋገጥ አንችልም። የእኛ እዚህ መኖር የእናንተ ድጋፍ ካልታከለበት ዋጋ የለውም፣ " በማለት ነዋሪውን ሲቀሰቅሱ እንደነበር ሆኖም ከህዝቡ ምንም ምላሽ እንዳላገኙ ገልጸዋል።

በህዝቡ ዝምታ የተደናገጠው የክልሉ መንግስት ሰኞ ሚያዚያ 23 ቀን 2004 ባደረገው ዝግ ስብሰባ " ዛሬ ሃሙስ ሚያዚያ 25 ነዋሪው  ወደ አደባባይ በሰልፍ በመውጣት ድርጊቱን እንዲያወግዝ እንዲሁም የልማት እንቅስቃሴው በፈቃዳችን የሚካሄድ እንጅ ያለፍላጎታችን የሚካሄድ አይደለም በማለት ጎዳና ላይ ወጥቶ ድጋፉን እንዲገልጽና የመገናኛ ብዙሀን ሽፋን እንዲሰጠው ውሳኔ አሳልፎአል።

በቤንሻንጉል ጉምዝም ህዝብ ተቃውሞውን ለመግለጽ መሳሪያ ለማንሳት እንደተገደደና ጥቃት እየሰነዘረ የሚሰወር ሃይል በተደጋጋሚ መታየቱ በሰፊው ይነገራል።

ወያኔ በኦጋዴን ክልል የተነሳውን የሙብት ጥያቄ ለመጨፍለቅ ወታደራዊ ሃይል በማሰማራት ሰላማዊ ዜጎችን የሽብርተኛ ድርጅት ደጋፊዎች ናችሁ እያለ ዘግናኝ ሰቆቃ እየፈጸመባቸው እንደሆነና አካባቢውን ለማንኛውም አይነት ሰብ አዊ እርዳታ ዝግ በማድረግ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች በረሃብ አለንጋ እንዲረግፉ እያደረገ መሆኑ በተለያዩ ሚዲያዎች መዘገቡ አይዘነጋም።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳውን የሙብት ጥያቄ በሃይል ለመጨፍለቅ እርምጃ መውሰዱን ቀጥሎበታል። 10 ወጣቶች በተቀነባበረ የሃሰት ክስ ፍርድ ቤት ቀረቡ።

ከወራት በፊት በአወልያ የተነሳው የእምነት ነጻነት ይከበር ጥያቄ እየተስፋፋ ሄዶ መላው አገሪቱን እያዳረሰ ባለበት ሰአት የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአንዳንድ አካባቢዎች የሀይል እርምጃ መውሰድ ጀምሮአል።

በምእራብ አርሲ ዞን አሳሳ ወረዳ 4 የእስልምና እምነት ተከታዮች ባለፈው ሳምንት በፌደራል ፖሊስ አባላት ከተገደሉ በሁዋላ ፣የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳውን የመብት ጥያቄ ያስተባበራሉ በሚል ፍራቻ ሰላማዊ ዜጎችን በአክራሪነት በመፈረጅ ማዋከብና ማሰሩ እንደተጀመረ በዚህም ምክንያት በአሳሳ አርሲ በርካቶች ታስረው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎአል። በአዲስ አበባ ከተማም ለቡ ኢምራን መስጂድ ውስጥ 10 የሚሆኑ ወጣት ምዕመናን እረብሻ አስነስተዋል በሚል የፈጠራ ክስ ተይዘው እንደታሰሩና በትናንትናው ዕለት  ጎፋ አንደኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ላይ እንደቀረቡ ለማወቅ ተችሎአል።

የግንባት 7 ዘጋቢ ወጣቶቹ የተከሰሱበትን የወንጀል ዝርዝር ሲገልጽ ከአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት መስጊዱን እንዲረከቡ የተወከሉትን ሼህ መሃመድ አማንን፣ እንዲሁም ርከክቡን ለማስፈጸም ከአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤትና ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፖሊስ የተወከሉ አባላትን አንደኛው ተከሳሽ እናንተ የመንግስት አጫፋሪዎች ናችሁ፤የቆማችሁትም ለመንግስት ፖለቲካ ነው፤እኛ የእስልምና መንግስት እስኪቋቋም እንታገላለን ሲላቸው ሌሎቹ ግብር አበሮቹ አላህ ወክበር በማለት አጅበውታል የሚል ነው።

በዚሁ ወጣቶቹ በተከሰሱበት የወንጀል ዝርዝር ስር እንደተመለከተው የመጅሊስ አባላት የሆኑት ሼህ መሃመድ አማን፣አቶ ይማም ሲራጅ፣ሼህ መሃመድ ሲራጅና ሼህ ሚስባ በድሩ ለሀሰት ምስክርነት ተቆጥረውባቸዋል።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ዘጋቢያችን የጠየቃቸውና ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ እኛ ጥያቄአችን አጭርና ግልጽ ነው - ባልመረጥናቸው የመጅሊስ አባላት አንመራም የሚል።ዘረኛውና ከፋፋዩ የወያኔ መንግስት ግን ይህንን ተፈጥሯዊ መብታችንን በመጨፍለቅ አዲስ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሃይማኖት ካልጫንኩባችሁ ብሎ እየተፍጨረጨረ ነው። በዚህም ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ ብሎም ከሙስሊሙ ከራሱ ጋር በመከፋፈል የዚህን የግፈኛ ስርዓት ዕድሜ የሚያራዝም መስሎታል፤ በእርግጠኝነት የምናገረው ይህ ጊዜ ያለፈበት የከሰረ ዘዴ እንደማይሰራለት ነው። ምክንያቱ ደግሞ ይህ አዲሱ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት በአንድም ኢትዮጵያዊ  የእስልምና እምነት ተከታይ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑነው ብለዋል።

ሌላ አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው ሰሞኑን ዘረኛው መለስ ዜናዊ ለፓርላማ ተብዬው የሰጠውን መግለጫ ተከትሎ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ተከታታይ ጥቃቶች እየተሰነዘሩ ነው። ይህም ክስ የዚሁ ጥቃት ተቀጥላ ሲሆን በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ፍርሃት ለመልቀቅና ጥያቄዎቹን ለማኮላሸት የተሸረበ የተለመደው ተራ የወያኔ ሴራ ነው በማለት አብራርተዋል።

ጸረ ህዝብ የሆነው ዘረኛው ወያኔ በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ የሚያካሂደውን ጥቃት በማባባስ ባለፈው አርብ በአርሲ አሳሳ ነፍሰ ገዳይ የአግዓዚ ጦር ወታደሮቹን በማሰማራት ከሶላት  ስግደት በሚመለሱ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ጥይት በማርከፍከፍ በወሰደው  እርምጃ  ከአምስት  በላይ  ንጹሃን  ሰዎች  ሲገደሉ  በርካቶች መቁሰላቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## የወያኔ የይስሙላ ፍርድ ቤት ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን በ2 ሺ ብር ሲቀጣ በፈጠራ ሽብርተኝነት ወንጀል እስር ቤት በመማቀቅ ላይ በሚገኘው ክንፈሚካ ኤል ደበበ ላይ የ8 ወራት እስራት ፈረደ

በእነ እንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ በፌዴራል አቃቤ- ሕግ አቤቱታ የቀረበበት የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የሁለት ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት ባለፈው ሰኞ ከሰዓት በኋላ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ተፈረደበት፡፡

ፍርድ ቤቱ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት በእስር ላይ የሚገኘውን 5ተኛ ተከሳሽ ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ከማረሚያ ቤት እንዲመጣ በማድረግ የስምንት ወር እስር የበየነበት ሲሆን የነጋድራስ ጋዜጣን ዋና አዘጋጅ ሱራፌል ግርማን በነፃ አሰናብቷል፡፡

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ እና ሱራፌል ግርማ ሰኞ ሚያዚያ 22 ጠዋት ችሎት ቢቀርቡም ፍርድ ቤቱ 5ተኛ ተከሳሽ ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ለምን አልቀረበም ሲል የማረሚያ ቤት ተወካይን ጠይቆ፣ ተወካዩዋ “እርሱ በአስረጅነት ስለተጠራ መምጣት ያለበት ስላልመሰለኝ ነው፣ የኔ ጥፋት ነው ከሰዓት በኋላ አመጣዋለሁ” በማለቷ ፍርድ ቤት ተብዬው ችሎቱን ለቀኑ 8:30 ሰዓት አስተላልፏል፡፡

ችሎቱ በከሰዓት በኋላ ቆይታው የአበበ ቀስቶን ከማረሚያ ቤት መምጣት አረጋግጦ የፌዴራል ዐቃቤ ህግ የአቀረበውን አቤቱታዎችና የጋዜጠኞቹ መልስ በቁንጽል ካሰማና አቶ ክንፈ ሚካኤልም የሰጡትን ጽሁፉ የኔ የራሴ ነው ማለቱን ተናግሮ ትዕዛዝ ማስተላለፉን ገልጸአል፡፡

ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤት ዘገባና አፃፃፍን መመርመሩን ገልፆ ጋዜጦቹ ያስተናገዷቸውን ጽሑፎች በሦስት ክፍሎ መመልከቱን አብራርቷል፡፡ “በችሎት በቀጥታ እየታየ ያለ ነገሮችን መዘገብ” ፣ “በችሎት መታየቱ ያበቃ ነገሮችን ዘገባ” እና “በችሎት የሚታዩትን ጉዳዮች ተንተርሶ የሚዘገቡ” ዘገባዎች በማለት ከፍሎ ማየቱን ጠቅሶ፣ የእስክንድር ነጋን የተከሳሽነት ቃል ተንተርሶ የወጣው የችሎት ዘገባ ሳይጨመር ሳይቀነስ በፍርድ ቤት የተባለው የወጣ በመሆኑ  የዐቃቤ ህግ አቤቱታን ውድቅ አድርገነዋል፣ በዚህ ሁሉቱም ጋዜጦች ነፃ ናቸው ብሏል፡፡ በዚህም የነጋድራስ ጋዜጣን ዋና አዘጋጅ በነፃ ተሰናብቷል።

በሁለተኝነትም ችሎት የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የወጣው የአንዷለም አራጌን ጽሑፍ ተመልክቷል። በዚህ ጉዳይ ላይም ተከሳሽ አንዷለም አራጌ በማረሚያ ቤቱ ላይ አቤቱታ አቅርበው ማረሚያ ቤቱም መልስ እንደሰጠበት የታወቀ ነው ስለዚህ ይሄ ጽሑፍ በፍርድ ቤቱ ላይ ምንም ችግር አይፈጥርም በማለት ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቷል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ  በችሎት እየታየ ባለ ጉዳይ ላይ የተፃፈው የናትናኤል መኮንን እና የክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ጽሑፍ የሚመለከት ነው ያለ ሲሆን፣ ናትናኤል ከርከሩን ከፍርድ ቤት አውጥቶ ወደ ጋዜጣ መውሰዱን፣ ተከሳሽ ይህን ያወጣው ፍርድ እንዲሰጠው አለመሆኑን፤ አበበ ቀስቶ ደግሞ በፍርድ ቤት የተያዘን ጉዳይ የህግ አመኔታ እንዳያገኝ ያደረገ በመሆኑ  የፍትህ ጋዜጣን ተጠቅሞ የፍርድ ቤት ሥራን በማወኩ ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡

በዚህ የተነሳ የአበበ ቀስቶ ድርጊት ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣና በገንዘብም 3 ሺህ ብር የሚያስቀጣ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የ8 ወር እስራት በይኖበታል በማለት የመሐል ዳኛ እንዳሻው አዳነ ውሳኔውን አንብቦአል። ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ዋና አዘጋጅ እንደመሆኑ የፕሬስ ሥራ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ይሄን በአግባቡ ባለመወጣት በእስር እስከ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ቢሆንም የጋዜጣውን ህዝባዊ የፕሬስ ሥራ አገልግሎት ከግምት በማስገባት እስራቱ ወደ ገንዘብ እንዲቀየር በመወሰን  2 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት ተወስኖበታል ብሎአል።

ችሎቱ ከተበተነ በኋላም ሁለት ሺህ ብር የመክፈሉ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org